በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የታክስ፣ ፍሬ ግብር እና ወለድ ምህረት አሰጣጥ ዝርዝር

አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር -----/2019

….../2019 ዓ.ም

አዲስ አበባ

መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 202/2018 አንቀጽ 42 እና በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009 አንቀጽ 12 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ይህንን መመሪያ አወጣ።

ክፍል አንድ፣ ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የታክስ፣ ፍሬ ግብር እና ወለድ (ቅጣትና ወለድ) ምህረት አሰጣጥ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር .../2019» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **መነሻ ሕግ እና ስልጣን**

ይህ መመሪያ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009 አንቀጽ 12 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 202/2018 አንቀጽ 42 መሠረት ለፋይናንስ ቢሮ በተሰጠው ሥልጣና ተግባር መሠረት ተዘጋጅቷል።

3. **ዓላማ**

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዋና ዋና ዓላማዎች ይኖሩታል፡

1. **ግብር ከፋዮች በተለያዩ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የሚደርስባቸውን የታክስ ዕዳ ጫና በመገምገም ግልጽ፣ ፍትሃዊ እና ወጥ የሆነ የምህረት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፤**
2. **የዕዳ ምህረት ጥያቄዎችን በባለሙያ ደረጃ የሚመረምር፣ የሚያጣራ እና የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ ግልጽ የአሠራር ማዕቀፍ መዘርጋት፤**
3. **የመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ፍትሃዊ እንዲሆን በማድረግ የግብር ከፋዮችን ሕጋዊ ማበረታቻ እና ቀጣይነት ማረጋገጥ።**

4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ንግድ ፍቃድ ያወጣ እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ታክስ ከፋይ ሆኖ ተመዝግቦ በሚንቀሳቀስ እና ከአቅም በላይ በሆነ

ምክንያት ሕጋዊ የታክስ ግዴታውን መወጣት ባለመቻሉ ምክንያት የዕዳ ምህረት ጥያቄ ባቀረበ ማንኛውም ግብር ከፋይ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፤ ሆኖም በሕገ-ወጥ መንገድ የታክስ ስወራ በፈጸሙ አካላት ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

5. **ትርጓሜ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡

1. «ቢሮ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ ነው፤
2. «ገቢዎች ቢሮ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ነው፤
3. «ካቢኔ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ነው፤
4. «ፍሬ ግብር» ማለት በሕግ መሠረት መከፈል ያለበት ዋናው የግብር መጠን ነው፤
5. «ወለድ (ቅጣትና ወለድ)» ማለት በታክስ ሕጎች መተላለፍ ወይም ዘግይቶ በመክፈል ምክንያት የሚጣል የገንዘብ መቀጮ እና ወለድ ነው፤
6. «ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት» ማለት በሰው እጅ ሊቆጣጠሩት በማይችሉ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ አደጋዎች የተነሳ ግብር ከፋዩ ሕጋዊ ግዴታውን መወጣት ሳይችል ሲቀር የሚከሰት ያልተጠበቀ ሁኔታ ነው፤
7. «ኮሚቴ» ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 መሠረት የሚቋቋመው የዕዳ ምህረት መርማሪ ኮሚቴ ነው፤

ክፍል ሁለት፡ ቅድመ-ሁኔታዎች እና ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

6. **የገቢዎች ቢሮ ቅድመ ማረጋገጫ**

1. ማንኛውም የዕዳ ምህረት (ፍሬ ግብር እና ወለድ) ጥያቄ ከማቅረቡ በፊት ግብር ከፋዩ አስቀድሞ በገቢዎች ቢሮ በኩል ፍሬ ግብር ፣የቅጣት እና ወለድ ምህረት ማግኘት የሚገባው መሆኑን የሚያረጋግጥ ቴክኒካዊ ግምገማ እና የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት አለበት።
2. በገቢዎች ቢሮ ያልተረጋገጠ ወይም የታክስ አስተዳደር አዋጅን መሠረት ያላደረገ የምህረት ጥያቄ በፋይናንስ ቢሮ ተቀባይነት አይኖረውም።

7. **ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ማረጋገጫ ዝርዝር**

ግብር ከፋዩ ያቀረበው የምህረት ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ በሚከተሉት ምክንያቶች የተነሳ ጉዳት መድረሱን ሕጋዊ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት፡

1. **ጎርፍ ወይም መሬት መንሸራተት ሲከሰት፡**

ሀ/ በሚመለከተው ማዘጋጃቤት ወይም በእሳት አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ጉዳት የደረሰው ንብረት ያለበትን ወረዳ እና የጉዳት መጠን ተገልጸ የተሰጠ መረጃ፤

ለ/ ከክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አደጋው ስለመድረሱና የወደመ ንብረት መጠን፣ አደጋው የደረሰበት ቦታ እና ሰዓት ተገልጸ የተሰጠ መረጃ፤

ሐ/ ከወረዳው አስተዳደር የተሰጠ አደጋው መድረሱን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ።

2. **እሳት ቃጠሎ ሲከሰት፣**

ሀ/ በሚመለከተው ማዘጋጃቤት ወይም በእሳት አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ጉዳት የደረሰው ንብረት ያለበትን ወረዳ እና የጉዳት መጠን ተገልጸ የተሰጠ መረጃ፤

ለ/ ከክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ አደጋው ስለመድረሱና የወደመ ንብረት መጠን፣ አደጋው የደረሰበት ቦታ እና ሰዓት ተገልጸ የተሰጠ መረጃ፤

ሐ/ ከወረዳው አስተዳደር የተሰጠ አደጋው መድረሱን የሚያረጋግጥ የድጋፍ ደብዳቤ።

3. **ንግድ ድርጅት ኪሳራ ወይም አቅም ማነስ ሲያጋጥም፣**

ሀ/ በሕጋዊ ሥልጣን በተሰጠው ፈቃድ ባለው ባለሙያ (Auditor) የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርት እና የፋይናንስ ኪሳራ መግለጫ።

4. **ከባድ ህመም ወይም አካል ጉዳት ሲያጋጥም፣**

ሀ/ በህክምና ተቋም የተረጋገጠ የህክምና ሰርተፍኬት እና ለህክምናው የወጡ የክፍያ ሰነዶች፤

ለ/ የህመሙ ዓይነት እና በቀጣይ የሚስፈልጉ ህክምናዎችን የሚገልጽ መረጃ፤

ሐ/ ከሚኖርበት ወረዳ ወይም ከሚመለከተው አካል በህመም ምክንያት የደረሰባቸውን የኢኮኖሚ ውድቀት የሚያሳይ የድጋፍ/የትብብር ደብዳቤ።

ክፍል ሦስት፣ የምህረት ጥያቄዎች የስልጣን ገደብ (ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ)

8. **ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ስለሆኑ የዕዳ ምህረት ጥያቄዎች**

1. ከብር 5,000,000 በላይ የሆኑ የዕዳ ምህረት ጥያቄዎችን ቢሮው ተቀብሎ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ማጣሪያ ያደርጋል።

2. ቢሮው ጉዳዩን መርምሮ ለውሳኔ አሰጣጥ አስፈላጊ ከሆኑ መረጃዎች እና ከራሱ የውሳኔ ሐሳብ ጋር ለካቢኔ ያቀርባል፤ ውሳኔውም በካቢኔ ይሰጣል።

ክፍል አራት፡ የምህረት ጥያቄዎችን የሚመረምር ኮሚቴ አወቃቀር፣ ሥልጣን እና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት

9. **የኮሚቴው አቋም**

ቀረቡትን የምህረት ጥያቄዎች በባለሙያ ደረጃ መርምሮ የውሳኔ ሐሳብ ለማቅረብ የሚከተሉት የሥራ ክፍሎች የተወከሉበት 5 አባል ያሉት የዕዳ ምህረት መርማሪ ኮሚቴ በቢሮው ኃላፊ ይሰየማል፡

1. የመንግስት ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ተወካይ — ሰብሳቢ፤
2. የመንግስት በጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ተወካይ — አባልና ጸሐፊ፤
3. ከፋይናንስ ቢሮ ህግ አገልግሎት ክፍል ተወካይ — አባል፤
4. ከፊስካል ፖሊሲ እና ገቢ ጥናት ዳይሬክቶሬት ተወካይ — አባል፤
5. አግባብነት ካለው የስራ ክፍል ተወካይ — አባል፤

10. **የኮሚቴው ሥልጣን እና ተግባር**

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡

1. ግብር ከፋዮች የሚያቀርቧቸውን የምህረት ጥያቄዎች እና ደጋፊ ሕጋዊ ሰነዶች መመርመር፤
2. የቀረቡት ምክንያቶች ከታክስ አስተዳደር አዋጅ እና ከዚህ መመሪያ ጋር መጣጣማቸውን ማረጋገጥ፤
3. የተሟላ የድጋፍ እና የምርመራ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቢሮ ኃላፊው ወይም ለካቢኔ የውሳኔ ሐሳብ ማቅረብ።

11. **የኮሚቴው የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት**

1. የኮሚቴው ስብሰባ የሚካሄደው ከጠቅላላ አባላት መካከል 2/3 (ሁለት ሦስተኛ) አባላት ከተገኙ ብቻ ነው።

2. ኮሚቴው የታክስ ጥያቄው በቀረበ በ15 ቀናት ውስጥ ለቢሮ ኃላፊው የውሳኔ ሀሳብ ያቀርባል።

3. የቢሮ ኃላፊው ኮሚቴው የውሳኔ ሀሳቡን ባቀረበ በ5 ቀናት ውስጥ ውሳኔውን በማጽደቅ ወይም በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።
4. በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ልዩነት ያለው አባላት ሃሳባቸውን በጽሁፍ በቃለ-ጉባኤ እንዲያዝላቸው የማድረግ መብት አላቸው።

ክፍል አምስት፡

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

12. **ክትትል እና ቁጥጥር**

ቢሮው በዚህ መመሪያ መሠረት የተደረጉ የዕዳ ምህረቶችን አፈጻጸም በተመለከተ መዝገብ ማደራጀት፣ በየወቅቱ መከታተል እና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

13. ***መመሪያውን ስለማሻሻል***

ይህ መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ እና እንደ ሐገራዊ ወይም ከተማ አስተዳደራዊ ሁኔታዎች በቢሮው ሊሻሻል ይችላል።

14. ***ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች***

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ፣ ሰርኩለር ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

15. ***መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ***

ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊው ተፈርሞ ከታተመበት/ከሰፈረበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡

አብዱልቃድር ሬድዋን ሁሴን

በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የፋይናንስ ቢሮ ኃላፊ

.....2019 ዓ.ም

አዲስ አበባ

«በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የታክስ፣ ፍሬ ግብር እና ወለድ ምህረት አሰጣጥ ዝርዝር አፈፃፀም ረቂቅ መመሪያ ቁጥር .../2019» ማብራሪያ/መግለጫ

1. መግቢያ እና የሕጉ መጠሪያ

- **የሕጉ ሙሉ መጠሪያ፡** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ የታክስ፣ ፍሬ ግብር እና ወለድ (ቅጣትና ወለድ) ምህረት አሰጣጥ ዝርዝር አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር .../2019
- **አቅራቢው አካል፡** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ቢሮ
- **የቀረበበት ዓላማ፡** በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የታክስ ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የሚያቀርቡትን የታክስ፣ ፍሬ ግብር፣ ቅጣትና ወለድ ምህረት ጥያቄዎች በግልጽ፣ ፍትሐዊና ወጥ በሆነ መልኩ መርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል አሠራርና በመዘርጋት መልካም አስተዳዳር ማስፈን ።

2. የሕጉ አስፈላጊነትና መነሻ ምክንያት

- **የሕግ መነሻና ሥልጣን፡** በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 51/2009 አንቀጽ 12 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 202/2018 አንቀጽ 42 መሠረት ለፋይናንስ ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የተዘጋጀ ነው።
- **መነሻ ምክንያት፡**
    1. ግብር ከፋዮች በተፈጥሮአዊ ወይም ሰው ሠራሽ አደጋዎች፣ በፋይናንስ ኪሳራ ወይም በጤና መታወክ ምክንያት የታክስ ግዴታቸውን መወጣት ሳይችሉ ሲቀሩ የሚደርስባቸውን የዕዳ ጫና ለመቀነስ ፍትሐዊ የመፍትሔ ሥርዓት ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ፤
    2. የዕዳ ምህረት ጥያቄዎችን በቴክኒክና በባለሙያ ደረጃ የሚያጣራና የሚያስረዳ ግልጽ የአሠራርና የኮሚቴ ማዕቀፍ ባለመኖሩ መመሪያ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
    3. የታክስ አሰባሰብ ሥርዓቱን ፍትሐዊነት በመጠበቅ ሕጋዊና ታማኝ ግብር ከፋዮችን ማበራታትና የንግድ ሥራቸውን ቀጣይነት ማረጋገጥ በመስፈለጉ።

3. የሕጉ ዋና ዋና ዓላማዎች

1. **ፍትሐዊ አሠራር መዘርጋት፡** ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የታክስ ዕዳ ውስጥ ለወደቁ ግብር ከፋዮች ግልጽ፣ ፍትሐዊና ወጥ የሆነ የምህረት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት።
2. **የምርመራ ማዕቀፍ መፍጠር፡** የዕዳ ምህረት ጥያቄዎችን በባለሙያ ደረጃ የሚመረምር፣ የሚያጣራና የውሳኔ ሐሳብ የሚያቀርብ የቴክኒክ ኮሚቴና አሠራር መዘርጋት።
3. **የንግድ ቀጣይነትን ማረጋገጥ፡** የመንግሥት ገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ሳይጎዳ የግብር ከፋዮችን ሕጋዊ ማበረታቻና ዘላቂ ቀጣይነት ማረጋገጥ።

4. የሕጉ ዋና ዋና ይዘቶች ዝርዝር ማብራሪያ

ረቂቅ መመሪያው አምስት (5) ክፍሎችና 15 አንቀጾችን ያካተተ ሲሆን ዋና ዋና ይዘቶቹ እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡-

ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 1 - 5)

- **የተፈጻሚነት ወሰን (አንቀጽ 4)፡** መመሪያው በከተማው ንግድ ቢሮ ፈቃድ አውጥተውና በገቢዎች ቢሮ ተመዝግበው በሚንቀሳቀሱ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የዕዳ ምህረት ጥያቄ ባቀረቡ አካላት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። **ነፃ ክፍተት/ልዩ ሁኔታ፡** በሕገ-ወጥ መንገድ የታክስ ስወራ በፈጸሙ አካላት ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።
- **ትርጓሜዎች (አንቀጽ 5)፡** «ፍሬ ግብር»፣ «ወለድ (ቅጣትና ወለድ)»፣ «ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት» እና «ኮሚቴ» የመሳሰሉ አስፈላጊ ፅንሰ-ሐሳቦች ግልጽ ትርጓሜ ተሰጥቷቸዋል።

ክፍል ሁለት፡ ቅድመ-ሁኔታዎች እና ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች (አንቀጽ 6 - 7)

- **የገቢዎች ቢሮ ቅድመ ማረጋገጫ (አንቀጽ 6)፡** ማንኛውም የዕዳ ምህረት ጥያቄ ወደ ፋይናንስ ቢሮ ከመምጣቱ በፊት በቅድሚያ በገቢዎች ቢሮ በኩል ቴክኒካዊ ግምገማ ተደርጎበት የድጋፍ ደብዳቤ ማግኘት አለበት።
- **የምክንያቶችና ማስረጃዎች ዝርዝር (አንቀጽ 7)፡** «ከአቅም በላይ ለሆኑ ምክንያቶች» ግልጽ የማስረጃ መስፈርት ተቀምጧል፡

- **ጎርፍ/መሬት መንሸራተት እና እሳት ቃጠሎ፡** ከማዘጋጃ ቤት/እሳት አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣ ከክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ እና ከወረዳ አስተዳደር የተሰጡ የድጋፍና የማረጋገጫ ደብዳቤዎች።
- **ንግድ ድርጅት ኪሳራ፡** ፈቃድ ባለው ኦዲተር የተረጋገጠ የኦዲት ሪፖርትና የፋይናንስ ኪሳራ መግለጫ።
- **ከባድ ሕመም/አካል ጉዳት፡** የሕክምና ሰርተፍኬት፣ የክፍያ ሰነዶች እና ከወረዳው የተሰጠ የኢኮኖሚ ውድቀትን የሚያሳይ ደብዳቤ።

ክፍል ሦስት፡ የምህረት ጥያቄዎች የሥልጣን ገደብ (አንቀጽ 8)

- **ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ የሆኑ ጥያቄዎች፡** ከብር 5,000,000 (አምስት ሚሊዮን ብር) በላይ የሆኑ የታክስ ዕዳ ምህረት ጥያቄዎችን ፋይናንስ ቢሮው መርምሮ የቴክኒክ የውሳኔ ሐሳብ ከተሟላ መረጃ ጋር **ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ** የሚያቀርብ ሲሆን ውሳኔውም በካቢኔ ይሰጣል።

ክፍል አራት፡ የኮሚቴው አወቃቀር፣ ሥልጣን እና አሠራር (አንቀጽ 9 - 11)

- **የኮሚቴው ስብጥር (አንቀጽ 9)፡** 5 አባላት ያሉት የዕዳ ምህረት መርማሪ ኮሚቴ በቢሮ ኃላፊው ይሰየማል (የመንግሥት ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት [ሰብሳቢ]፣ የበጀት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት [ጸሐፊ]፣ ሕግ አገልግሎት፣ ፊስካል ፖሊሲና ገቢ ጥናት፣ እና አግባብነት ያለው ሥራ ክፍል)።
- **የጊዜ ገደብና የውሳኔ ሂደት (አንቀጽ 11)፡**
  - ምህረት ጥያቄው በቀረበ በ 15 ቀናት ውስጥ ኮሚቴው ምርመራውን አጠናቆ ለቢሮ ኃላፊው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።
  - የቢሮ ኃላፊው የውሳኔ ሐሳቡ በደረሰው በ 5 ቀናት ውስጥ በማጽደቅ፣ በማሻሻል ወይም በመሻር ውሳኔ ይሰጣል።
  - ምልአተ ጉባኤው 2/3ኛ አባላት ሲገኙ ይሆናል።

ክፍል አምስት፡ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 12 - 15)

- **የተደረጉ ምህረቶች መዝገብ ተይዞ ክትትልና ቁጥጥር እንደሚደረግ፣ ተቃራኒ አሠራሮች ተፈጻሚነት እንደሌላቸው እና መመሪያው በቢሮ ኃላፊው ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና እንደሚሆን ይደነግጋል።**